# Have you heard of the Four Spiritual Laws?

# ስለ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰምተሃልን?

There are natural laws that control the world in which we live. There are also spiritual laws which determine your relationship with God.

ተፈጥሮአዊ ሕግ የምንኖርበትን ዓለም እንደሚቆጣጠረው መንፈሳዊ ሕግ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት ይወስናል።

## 1 LAW ONE

GOD **LOVES** YOU AND OFFERS A WONDERFUL **PLAN** FOR YOUR LIFE.

**GOD'S LOVE**

*"God so loved the world that He gave His one and only Son, that whoever believes in Him shall not perish, but have eternal life." (John 3:16 NIV)*

**GOD'S PLAN**

*"Peace I leave with you; my peace I give you. I do not give to you as the world gives. Do not let your hearts be troubled and do not be afraid." (John 14:27)*

Not all people are experiencing the abundant life, because…

## 1 1ኛው ሕግ

**እግዚአብሔር ስለሚወድህ ለሕይወትህ አስደናቂ የሆነ እቅድ ሰጥቶሃል።**

**የእግዚአብሔር ፍቅር**

*«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» ዮሐ. 3፥16*

**የእግዚአብሔር ዕቅድ**

*«ሰላምን እተውላችኋለሁ ፣ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም ፤ ልባችሁ አይታወክ አይፍራም።» ዮሐ. 14፥27*

ሰው ሁሉ የተትረፈረፈ ሕይወትን አይለማመድም ምክንያቱም…

## 2 LAW TWO

PEOPLE ARE SINFUL AND SEPARATED FROM GOD SO WE CANNOT KNOW AND EXPERIENCE GOD'S LOVE AND PLAN FOR OUR LIFE.

**PEOPLE ARE SINFUL**

*"All have sinned and fall short of the glory of God." (Romans 3:23)*

People were created to be friends with God; but we chose to go our own way, and friendship with God was broken. This is what the Bible calls sin. This is shown

(1) when we rebel against God,
(2) when we do not care about God and
(3) when we do not live up to God's perfect standard.

## 2 2ኛው ሕግ

**ሰው ሁሉ ኃጢአተኛና ከእግዚአብሔር የተለየ ነው። ስለዚህም እኛ የእግዚአብሔርን ፍቅር ማወቅ ፣ መለማመድና ለሕይወታችንም ያለውን ዓላማ መረዳት አንችልም።**

**ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ነው።**

*«ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።» ሮሜ 3፥23*

ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ እንዲሆን ተፈጥሮ ነበር ፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ የገዛ መንገዱን ስለተከተለ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ወዳጅነት ተቋረጠ። ይህንን ነው መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት እያለ የሚጠራው። ይህም በሚከተለው ይገለጻል ፦

1. በእግዚአብሔር ላይ ስናምጽ
2. ለእግዚአብሔር ግድ ሳይኖረን ሲቀርና
3. ፍጹም በሆነው በእግዚአብሔር መመዘኛ መሠረት ኖረን ሳንገኝ ስንቀር

### PEOPLE ARE SEPARATED FROM GOD

*"The wages of sin is death"* [spiritual separation from God]. *(Romans 6:23)*




God is holy and people are sinful. There is a great separation between the two. The arrows show how people try to reach God and the abundant life through their own efforts: such as living a good life, being religious, helping others, etc.—but they always fail.

The third law gives the only answer to this problem…

## 3 LAW THREE

JESUS CHRIST IS THE **ONLY** WAY WE CAN REACH GOD. HE DIED FOR US. THROUGH HIM WE CAN KNOW GOD AND EXPERIENCE HIS LOVE AND PLAN FOR OUR LIFE.

### HE DIED AND ROSE FROM THE DEAD

*"For Christ died for sins once for all, the righteous for the unrighteous, to bring you to God." (1Peter 3:18)*

*"After His suffering, He showed himself to these men and gave many convincing proofs that He was alive. He appeared to them over a period of forty days and spoke about the kingdom of God." (Acts 1:3)*

### HE IS THE ONLY WAY

*"Jesus said to him, 'I am the way, and the truth, and the life; no one comes to the Father, but through Me.'" (John 14:6)*




God has bridged this separation between us and Himself by sending His Son Jesus Christ, to die on the cross in our place.

It is not enough just to know these three laws …

### ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ተለይቷል

*«የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው።» (በመንፈስ ከእግዚአብሔር መለየት) ሮሜ 6፥23*




እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ሰው ሁሉ ደግሞ ኃጢአተኛ ነው። በሁለቱም መካከል ታላቅ የሆነ መለያየት አለ። ይህ ቀስት የሚያመለክተው ሰው በራሱ ጥረት እንዴት ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ እንደሚሞክር ነው። ይኸውም ጥሩ የሆነ ኑሮ በመኖር ፣ ኃይማኖተኛ በመሆን ፣ ሌሎችን በመርዳት… ነገር ግን በሁሉም ጥረቱ ወደቀ።

3ኛው ሕግ ለዚህ ችግር መልስ ይሰጠናል።

## 3 3ኛው ሕግ

**ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ብቸኛ መንገድ ነው። እርሱ ስለእኛ ሞቷል። በእርሱ በኩል እግዚአብሔርን ለማወቅ እና የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት እንደዚሁም ለሕይወታችን ያለውን ዕቅድ ለማወቅ እንችላለን።**

### እርሱም ሞቶ ከሞት ዳግመኛ ተነስቷል።

*«ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ አመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቷልና።» 1ኛ ጴጥ. 3፥18*

*«ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መን ግሥት ነገር እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ራሱን አሳያቸው።» የሐዋ. ሥራ 1፥3*

### መንገዱ እርሱ ብቻ ነው

*«እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።» ዮሐ. 14፥6*




እግዚአብሔር አምላክ በእኛና በእርሱ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥፋት ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በእኛ ፋንታ በመስቀል ላይ እንዲሞት ልኮታል።

**እነዚህን ሦስቱን ሕጎች ብቻ ማወቅ በቂ አይደለም።**

# 4

## LAW FOUR

WE MUST EACH **RECEIVE** JESUS CHRIST AS SAVIOUR AND LORD; THEN WE CAN KNOW AND EXPERIENCE GOD'S LOVE AND PLAN FOR OUR LIVES.

### WE MUST RECEIVE CHRIST THROUGH FAITH

*"As many as received Him, to them He gave the right to become children of God, even to those who believe in His name." (John 1:12)*

*"By grace you have been saved through faith; and that not of yourselves, it is the gift of God; not as a result of works, that no one should boast." (Ephesians 2:8,9)*

### WE RECEIVE CHRIST BY INVITING HIM INTO OUR LIVES

*"Behold, I stand at the door and knock; if any one hears my voice and opens the door, I will come in to him." (Revelation 3:20)*

It is not enough just to agree with Christ's teachings. Receiving Christ means turning to God from self (repenting). We trust Christ to come into our lives and to forgive us our sins. We let Him make us what he wants us to be.

**THESE TWO CIRCLES REPRESENT TWO KINDS OF LIVES:**




**SELF-CONTROLLED LIFE**

S – Self on the throne.

† – Christ outside the life.




**CHRIST-CONTROLLED LIFE**

† – Christ on the throne.

S – Self off the throne.

**Which circle best describes your life?**
**Which circle would you like to have represent your life?**

The following explains how you can receive Christ:

# 4

## 4ኛው ሕግ

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በመቀበል እግዚአብሔር አምላክ ለእኛ ያለውን ፍቅርና ዕቅድ ልናውቅና ልን ለማመድ እንችላለን።

### ክርስቶስን በእምነት መቀበል አለብን።

*«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው።» ዮሐ. 1፡12*

*«ፀጋው በእምነት አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጅ ከእናንተ አይደለም። ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።» ኤፌ 2፡8-9*

### ወደ ሕይወታችን እንዲመጣ በመጋበዝ ክርስቶስን እን ቀበለው።

*«እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ።» ራእይ 3፡20*

ከክርስቶስ ትምህርት ጋር መስማማቱ ብቻ በቂ አይደለም። ክርስቶስን መቀበል ማለት ከገዛ ራስ መንገድ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወታችን በመምጣት ኃጢአታችንን ይቅር እን ደሚለን እናምናለን። እርሱ እንደሚፈልገው ዓይነት ሰዎች እንዲያደርገን እንፍቀድለት።




**በእኔነት ቁጥጥር ሥር ያለ ሕይወት**

እ - እኔነት በሕይወት ዙፋን ላይ

† - ክርስቶስ ከሕይወት ውጪ




**በክርስቶስ ቁጥጥር ሥር ያለ ሕይወት**

† - ክርስቶስ በዙፋን ላይ

እ - እኔነት ከዙፋን ወርዶ

የትኛው ክብ ነው የአንተን ሕይወት የሚያመለክተው?
የትኛውስ ክብ የአንተን ሕይወት እንዲወክል ትፈልጋለህ?

የሚከተለው ሃሳብ ክርስቶስን እንዴት መቀበል እንደሚገባህ ያሳያል።

## YOU CAN RECEIVE CHRIST RIGHT NOW BY FAITH THROUGH PRAYER

Prayer is simply talking to God.

**"Lord Jesus, I want to know you as my personal Saviour. I thank you for dying on the cross in my place. I open the door of my heart and my life to you. I accept you as my Saviour and the Lord of my life. I thank you for giving me eternal life and forgiving my sins. Guide my life according to your will."**

Does this prayer express the desire of your heart?
If it does, let's pray together.

## ክርስቶስን አሁን አምነህ በጸሎት ልትቀበለው ትችላለህ።

ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው።

**ለመጸለይም ፈቃደኛ ከሆንክ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ የግል አዳኜ እንደሆንክ ላውቅህ እፈልግሃለሁ በእኔ ቦታ በመስቀል ላይ ስለሞትክልኝ አመሰግንሃለሁ። የልቤንና የሕይወቴን በር ከፍቼልሃለሁ። አዳኜና የሕይወቴ ጌታ መሆንህን ተቀብያለሁ። ሐጢአቴን ሁሉ ይቅር ስላልከኝና ዘላለማዊ ሕይወትን ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ። እንደፈቃድህም ሕይወቴን ምራ።**

ይህ ጸሎት የልብህን ፍላጎት ያሳያል?

ካሳየ አብረን እንጸልይ?

## DID YOU RECEIVE CHRIST INTO YOUR LIFE?

According to His promise in Revelation 3:20, where is Christ right now in relation to you? Christ said that He would come into your life. Would He mislead you? On what authority do you know that God has answered your prayer? (The trustworthiness of God Himself and His Word.)

## THE BIBLE PROMISES ETERNAL LIFE

*"The witness is this that God has given us eternal life, and this life is in His Son. He who has the Son has the life; he who does not have the Son of God does not have life. These things I have written to you who believe in the name of the Son of God, in order that you may know that you have eternal life." (1 John 5:11-13)*

Thank God often that Christ is in your life. He will never leave you (Hebrews 13:5). You can know on the basis of His promise that Christ lives in you and that you have eternal life from the very moment you invite Him in.

## ክርስቶስን በሕይወትህ ተቀብለኸዋል?

በራእይ 3 ፥20 በተሰጠው ተስፋ መሠረት በአሁኑ ሰዓት ክርስቶስ ኢየሱስ በየት ይገኛል? ክርስቶስ ወደ ሕይወትህ እንዲመጣ ከተናገረ የሚዋሽ ይመስልሃል? እግዚአብሔር ጸሎትህንም እን ደመለሰ በምን ታውቃለህ? (ምክንያቱም እግዚአብሔርና ቃሉ የታመነ ነው።)

## መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስን ለተቀበሉ ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል።

«እግዚአብሔር የዘለዓለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህንን ጽፌላችኋለሁ።» 1ኛ ዮሐ. 5፡11-13

ክርስቶስ ኢየሱስ በሕይወትህ ውስጥ ስላለ እግዚአብሔርን ዘወትር አመስግን። በዕብ. 13፡5 ላይ ከቶ እንደማይለይህም ይናገራል። ክርስቶስ በሕይወትህ እንደሚኖርና ከእርሱም የተስፋ ቃል የተነሳ የዘላለም ሕይወት እንዳለህ ልታውቅ ትችላለህ።

## DO NOT DEPEND ON FEELINGS

The Christian lives according to the Word of God, because the Word of God is our authority. The train diagram shows the relationship between the Word of God, faith and feelings.




1. Fact has the power to lead us.
2. We are bound together with the power of truth.
3. When we start obeying the truth our feelings will follow the right path. Therefore we should always depend on the sure foundation of the Word and not our feelings.

## በስሜቶች ላይ አትደገፍ

ክርስቲያን የሚኖረው በእግዚአብሔርና በቃሉ በመታመን ነው ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ለእኛ መመሪያችን ነው። የሚከተለው ባቡር መሰል ስዕላዊ መግለጫ በአንድ አማኝ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል ፣ እምነትና ስሜት እንዴት አንድነት እንዳለቸው ያሳያል።




1. እውነት ሊመራን የሚችል ኃይል አለው።
2. ከእውነት ኃይል ጋር በእምነት ተሳስረናል።
3. ለእውነት መታዘዝ ስንጀምር ስሜቶቻችን ሁሉ ትክክለኛውን ጐዳና መከተል ይጀምራሉ። ስለዚህ ሁልጊዜ በእውነተኛው የቃሉ መሠረት እንጅ በስሜቶቻችንን ላይ መደገፍ የለብንም።

## THE MOMENT THAT YOU RECEIVED CHRIST MANY THINGS HAPPENED:

1. Christ came into your life. (Revelation 3:20 ; Colossians 1:27)
2. Your sins were forgiven. (Colossians 1:14)
3. You became a child of God. (John 1:12)
4. You began the great adventure for which God created you. (John 10:10; 2 Corinthians 5: 14, 15, 17)

Can you think of anything more wonderful that could happen to you than receiving Christ? Would you like to thank God in prayer right now for what He has done for you?

By thanking God, you demonstrate your faith.
What is next?

## ክርስቶስን በተቀበልክበት ቅጽበት ውስጥ ብዙ ነገር ይፈጠራል።

1. ክርስቶስ ወደ ሕይወትህ ይመጣል። ራእይ 3፡20 ቆላስ. 1፡27
2. ኃጢአትህ በሙሉ ይቅር ተብሎአል። ቆላስ. 1፡14
3. የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል። ዮሐ. 1፡12
4. እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ፍቅርና ዕቅድ መለማመድ ትጀምራለህ። ዮሐ. 10፡10 ፣ 2ኛ ቆሮ. 5፡14, 15, 17

ክርስቶስን ከመቀበል የተሻለ ነገር በሕይወትህ ሊሆን እንደሚችል ታስባለህ? እግዚአብሔር ስላደረገልህ ሁሉ አሁን በጸሎት ልታመሰግነው ትወዳለህ?

በማመስገን እምነትህን አሳይ።
ከዚህ በኋላስ?

## SUGGESTIONS FOR CHRISTIAN GROWTH

Spiritual growth results from trusting Jesus Christ. A life of faith will enable you to trust God increasingly with every detail of your life, and to practice the following:

- **G**o to God in prayer daily. (John 15:7)
- **R**ead God's Word daily (Acts 17:11); begin with the Gospel of John.
- **O**bey God moment by moment. (John 14:21)
- **W**itness for Christ by your life and words. (Matthew 4:19; John 15:8)
- **T**rust God for every detail of your life. (1 Peter 5:7).
- **H**oly Spirit - allow Him to control and empower your daily life and witness. (Galatians 5:16,17; Acts 1:8)

## ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገት የሚረዱህ ነጥቦችን

የሚከተሉትን ሃሳቦች ሊረዱህ ይችላሉ።

- በየዕለቱ በፀሎት በእግዚአብሔር ፊት ቅረብ። ዮሐ. 15፡7
- የእግዚአብሔርንም ቃል በየዕለቱ አጥና። ሐዋ. 17፡11
- ጥናትህንም ከዮሐንስ ወንጌል ጀምር።
- በየደቂቃው ሁሉ እግዚአብሔርን ታዘዝ። ዮሐ. 14፡21
- በቃልና በሕይወት ስለ ክርስቶስ መስክር። ማቴ. 4፡19 ፣ ዮሐ. 15፡8
- ስለ እያንዳንዱ የሕይወት ጉዳይህ በእግዚአብሔር ላይ ታመን። 1ጴጥ. 5፡7
- መንፈስ ቅዱስ በየዕለቱ ሕይወትህንና ምስክርነትህን እንዲቆጣጠርና በኃይሉም እን ዲሞላ ፍቀድለት። ገላ. 5፡16-17 ፣ የሐዋ. ሥራ 1፡8

## THE NEED TO FELLOWSHIP IN CHURCH

The Bible tells us that it is important to meet together regularly with other Christians (Hebrews 10:25).

Have you ever watched a fire burning? Several logs together burn brightly. But if you pull one log away from the fire, its flame soon goes out. The same thing happens to us if we do not spend time with other Christians who have accepted Christ as their personal Saviour. Attend a church where Christ is talked about and the Bible is taught. Start this week and make plans to attend regularly.

If this article has been helpful to you, please give it or read it to someone else. This way you might help another person come to know God personally.

## በቤተክርስቲያን ህብረት የማድረግ አስፈላጊነት

ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አዘውትረን ህብረት ማድረግ ጠቃሚ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን 10 ፥25 ላይ ይነግረናል።

እንጨት ሲነድድ አይተህ ታውቃለህን? እንጨቶች በአንድነት ሲነድዱ ደማቅ የሆነ ብርሃንን ይሰጣሉ ነገር ግን አንዱን እንጨት ለብቻው ከሚነድደው እሳት ውስጥ አውጥተህ ብታስቀምጠው ወዲያውኑ ከእንጨቱ የሚታየው ብርሃን ይጠፋል። በክርስትና ሕይታችንም ከሌሎች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ከተቀበሉ ክርስቲያኖች ጋር ጊዜ አብረን የማናሳልፍ ከሆነ እንደዚሁ ይሆናል ማለት ነው። ኢየሱስን የምታከብርና መጽሐፍ ቅዱስንም ወደ እምታስተምር ቤተክርስቲያን ሂድ።

## WANT FURTHER HELP?

If you would like help in developing a closer relationship with Jesus Christ, please visit:

- www.hereslife.com/connect
- www.ichristianlife.com
- www.looktojesus.com
- www.growinginchrist.com
- www.basicsteps.org
- www.greatcom.org

This article is also available in many other languages from www.hereslife.com/tracts.

© 1985- 2008 Campus Crusade for Christ Australia A.C.N 002 310 796

AmhEng4pWBw0809

## ተጨማሪ እርዳታ ትፈልጋለህ?

ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዲኖርህ ተጨማሪ እርዳታን የምትፈልግ ከሆነ ፥ ከዚህ በታች ያለውን አድራሻ ተጠቀም።

የሕይወት አገልግሎት
መ.ሕ. ቤተ ክርስቲያን
የመ.ሳ.ቁ. 698
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ